የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ
ለንደን

**Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**LONDON**

## የሀዘን መግለጫ ጥሪ

## በለንደን ከተማና በአከባቢው ለምትገኙ ኢትዮጰያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣

ሚያዝያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም በሊብያ ራሱን ISIL ብሎ የሚጠራ አሸባሪ ቡድን በንፁሃን ዜጎቻችን ላይ የፈፀመውን ኢሰብአዊ እና ጭካኔ የተሞላበት አረመኔያዊ የግድያ ተግባርና በደቡብ አፍሪካ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያ ፣ ድብደባና ዘረፋ በጥብቅ በማውገዝ መንግስት ከሚያዝያ 16-18/2007 ዓ.ም ያሉት ሦስት ቀናት ብሔራዊ የሐዘን ቀናት ሆነው እንዲውሉና የሪፐብሊኩ ሰንድቅ ዓላማም ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ውሳኔ አስተላልፏል:: ድርጊቱን የአገራችን ሕዝቦች በከፍተኛ የሀዘን ስሜት እያወገዙ የሚገኙ ሲሆን፣ የተለያዩ አገራትም ይህን ኢሰብአዊ ድርጊት በጥብቅ በማውገዝ ላይ ይገኛሉ::

ስለሆነም በለንደን እና አከባቢው የምትኖሩ ኢትዮጰያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከ April 23 ፣ 24 እንዲሁም 27 ቀን 2015 ከጠዋቱ 9:30 AM – 4:30 PM በሚሲዮኑ ጽ/ቤት በመገኘት የተሰማችሁን ሃዘን እንድትገልፁ ሚሲዮኑ የሀዘን መግለጫ መዝገብ አዘጋጅቷል::

በተጨማሪም የሻማ ማብራት ስነስርዓት እሁድ April 26 ቀን 2015 በ5:00 PM በሚሲዮኑ ጽ/ቤት የተዘጋጀ በመሆኑ በፕሮግራሙ ላይ በመገኘት በዜጎቻችን ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ግድያ በጋራ እንድናወግዝና ለቤተሰቦቻቸውም የሀዘናቸው ተካፋይ መሆናችን እንድንገልፅ ኤማባሲው በአክብሮት ጥሪ ያስተላልፋል::

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ጽ/ቤት

ለንደን

17 PRINCES GATE
LONDON, SW7 1PZ
www.ethioembassy.org.uk

TEL: 020 7589 7212
FAX: 020 7584 7054
e-mail: info@ethioembassy.org.uk